የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# የተግባራትና የተገኙ ዐበይት ውጤቶች፡ ጭምቅ ሪፖርት

ከሐምሌ 2014 ዓ.ም. - ሰኔ 2015 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ)
# ተግባራትና የተገኙ ዐበይት ውጤቶች
# ሐምሌ 2014 ዓ.ም. - ሰኔ 2015 ዓ.ም.
# ጭምቅ ሪፖርት
# (የመጨረሻ ረቂቅ)

አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ
ነሐሴ 2015 ዓ.ም.

# ይዘት


1. መግቢያ ........ 1

2. ኢሰመኮ በጨረፍታ ........ 2

3. የሪፖርት ዘመኑ የዕቅድ አፈጻጸም አጠቃላይ ግምገማ ........ 9

3.1. የሰብአዊ መብቶች ትምህርት ........ 9

3.2. የስብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ ........ 11

3.3. የሴቶ እና የሕፃናት መብቶች ........ 14

3.4. አከል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች ........ 15

3.5. የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና የፍልሰተኞች መብቶች ........ 18

3.6. የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ........ 20

3.7. ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ........ 22

3.8. ኮሙኒኬሽን ኢ.ኮ.ቴ እና አጋርነት ........ 26

3.8.1. ሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ........ 26

3.8.2. ኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ........ 28

3.8.3. ፕሮግራምና አጋርነት ........ 29

3.9. ተቋማዊ ሪፎርም፣ ዐቅም ግንባታና ቀጣይነት ........ 31

3.9.1. ዋና ኮሚሽነር ጽ/ቤት ........ 31

3.9.2. የፋይናንስ እና አስተዳደር ........ 33

3.9.3. የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ........ 35

4. የሪፖርት ዘመኑ የበጀት ዕቅድ አፈጻጸም ማጠቃለያ ........ 36

5. በአፈጻጸም ያጋጠሙ ችግሮች ........ 37

# 1. መግቢያ

በዚህ ሪፖርት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት አቆጣጠር በ2015 ዓ.ም. ያከናወናቸው ዐበይት ተግባራት እና የተገኙ ውጤቶች ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም የኮሚሽኑን የፋይናንስ አጠቃቀም መግለጫ እና በዕቅድ አፈጻጸም ያጋጠሙ ችግሮች ትካትተዋል፡፡ ተግባራቱ ኮሚሽኑ በአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱ ለይቶ ባስቀመጣቸው ዘጠኝ የትኩረት መስኮች መሠረት የተደራጁ ናቸው፡፡

1. የሰብአዊ መብቶች ትምህርት
2. የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ
3. የሴቶችና የሕፃናት መብቶች
4. የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን መብቶች
5. የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ፍልሰተኞች መብቶች
6. የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች
7. የኢኮኖሚያዊ እና የማኅበራዊ መብቶች
8. የኮሙኒኬሽን፣ የመረጃና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና አጋርነት
9. ተቋማዊ ሪፎርም እና ዘላቂ ዐቅም ግንባታ ናችው፡፡

## 2. ኢሰመኮ በጨረፍታ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌዴራል ሕገ መንግሥቱ መሠረት ነጻ የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበርና እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው:: *(የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/14 እና ዐዋጅ ቁጥር 210/1992 በዐዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው)*

### ራዕይ

የሰብአዊ መብቶች ባህል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት

### ተልዕኮ

የሰብአዊ መብቶች ጥበቃን ለሁሉም ማረጋገጥ እና ማራመድ (ማስፋፋት)

### የኢሰመኮ እሴቶች

ለእኩልነት፣ ለሰው ልጅ ክብር እና ለፍትሕ ያለውን ቁርጠኝነት መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑ አንኳር እሴቶች፡-

- ተቋማዊ ነጻነት/ ገለልተኝነት፣
- አካታችነት፣
- ከሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች እና ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍል ጋር አጋርነት፣
- እውነተኝነት እና
- በሥነ ምግባር የታነጸ ናቸው::

### የኢሰመኮ መርሖች

- በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እና ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ሰብአዊ እና ሰብአዊነት መብቶች ሰነዶችና ሕግጋት መመራት፤
- ACHPR/Res.370(LX)2017 ለብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና በአፍሪካ ውስጥ በተለይ በሰብአዊ መብቶች ላይ ለሚሠሩ ተቋማት የአጋር ተቋም ደረጃን ለመስጠት በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የወጣ የአቋም መግለጫ፤ እንዲሁም
- ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማትን በሚመለከት የወጡ መርሖች (የፓሪስ መርሖች) ማዕቀፎች ውስጥ መንቀሳቀስ::

### የኢሰመኮ ዋና ዋና ዓላማዎች

- ሕዝቡ ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖረው ማስተማር፤
- ሰብአዊ መብቶች እንዳይጣሱ መጠበቅ እና ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤ እና
- ሰብአዊ መብቶቹ ተጥሰው ሲገኙ በምርመራ ይፋ እንዲሆኑ ማድረግና አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መከታተል ናቸው::

## የኢሰመኮ ሥልጣንና ኃላፊነት

በማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር 210/1992 እና በማሻሻያ ዐዋጅ ቁጥር 1224/2012 መሠረት ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣን እና ኃላፊነቶች ተሰጥቶታል፡፡

- ሰብአዊ መብቶች በማንኛውም ዜጋ፣ በመንግሥት አካላት፣ በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሌሎች ማኅበራት እንዲሁም በባለሥልጣኖቻቸው መከበራቸውን ማረጋገጥ፤
- በመንግሥት የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እንዲሁም ትእዛዞች ከሰብአዊ መብቶች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- ኅብረተሰቡ ስለሰብአዊ መብቶች በቂ ዕውቀት ኖሮት መብቱን የማክበርና የማስከበር ባህል እንዲያዳብር መገናኛ ብዙኃንና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር፤
- የሰብአዊ መብቶች መጣስ ቅሬታዎች ሲቀርቡለት ወይም በራሱ አነሳሽነት ምርመራ ማካሄድ፤
- በምክር ቤት ወይም በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ካሉ ጉዳዮች በስተቀር የሰብአዊ መብቶች መጣስን አስመልክቶ በማንኛውም ሰው የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ወይም በራሱ ተነሳሽነት ምርመራ ማካሄድ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውንም ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች ወይም በቁጥጥር ወይም በእገታ ሥር የሚገኙ ሰዎች ያሉበትን ስፍራ እንዲሁም እንደ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መጠለያ ጣቢያ፣ የገበያ ማእከል የመሳሰሉ እና የሕዝባዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ያለ ቅድመ ማስታወቂያ በመጐብኘት ስለሰብአዊ መብቶች ክትትል ማድረግና መከበራቸውን ማረጋገጥ፤
- ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉና አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ ማሳሰብ፤
- በሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት መስጠት፤
- ለዓለም አቀፍ አካላት በሚቀርቡ የሰብአዊ መብቶች ሪፖርቶች ላይ አስተያየት መስጠትና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስብሰባዎች፣ ኮንፈረንሶች ወይም ሲምፖዚየሞች ላይ መሳተፍ፤
- በምርጫ እንዲሁም በአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ወቅት የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅን ክትትል ማድረግ እና
- ኮሚሽኑ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ሁሉ እንዲያከናውን ሙሉ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## የሰብአዊ መብቶች ሥራ መሪዎች



ዶ/ር ዳንኤል በቀለ
የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር



ራኬብ መሰለ
የኢሰመኮ ምክትል ዋና ኮሚሽነር



ዶ/ር አብዲ ጅብሪል
የሲቪል፣ የፖለቲካ እና የማኅበረ ኢኮኖሚያዊ መብቶች ኮሚሽነር



ርግበ ገብረሐዋርያ
የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን መብቶች ኮሚሽነር



መስከረም ገስጥ
የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ኮሚሽነር

# የኢሰመኮ ተልዕኮ የትኩረት መስኮች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በ 7 መስኮች ላይ ትኩረት አድርጎ ይሠራል። እነርሱም፡-

### የሰብአዊ መብቶች ትምህርት

በስልጠናዎች፣ በዐቅም ግንባታዎች፣ በምስለ-ችሎት (moot court) ውድድሮች እና የሰብአዊ መብቶች ትምህርት በብሔራዊ የትምህርት ፖሊሲና ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንዲካተት የውትወታ ሥራዎች በመሥራት በሀገራችን ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ባህልን ማጠናከር፤ በባለመብቶችና በባለግዴታዎች ዘንድ ስለ ሰብአዊ መብቶች ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ማሳደግ።

### የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ

ዓለም አቀፍ እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች እየተከበሩ ስለመሆናቸው፤ ከአቤቱታ አቅራቢዎች ወይም በኮሚሽኑ ተነሳሽነት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምርመራ በማድረግ፤ የማረሚያ ቤቶችን እና ፖሊስ ጣቢያዎችን ክትትል በማድረግ፤ የመብት ጥሰት ደረሰባቸው ሰዎች መፍትሔ እንዲያገኙ እና መብት የጣሱ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ።

### የሴቶችና የሕፃናት መብቶች

የሴቶችንና የሕፃናትን መብቶች ማስፋፋት፣ ማክበርና ጥበቃ ማድረግ፤ ሕጎችን ማጥናትና ሥርዓታዊ የመብት ጥሰቶችን መመርመር፤ ሕጎችና አሠራሮች ከዓለም አቀፍና ከብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን መከታተል፤ የሴቶችና የሕፃናት መብቶች በሁሉም ደረጃ ባሉ አሠራሮች እንዲካተት ማድረግ።

### የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች

የአካል ጉዳተኞችን እና የአረጋውያንን መብቶች ማስፋፋት፤ የሚገጥሟቸውን ፈርጀ ብዙ ተግዳሮቶች በተመለከተ ግንዛቤ መፍጠር፤ ችግሮቻቸውም የብሔራዊ ፖሊሲ ቀረጻ አጀንዳ እንዲሆኑ ማድረግ፤ ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ብሔራዊ የሕግና የተቋማት ማሻሻያዎች እንዲደረጉ መሥራት።

## የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና የፍልሰተኞች መብቶች

የስደተኞችን፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችንና የፍልሰተኞችን መብቶች ማክበር፣ ማስከበር። እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸውን ጥበቃ እንዲያገኙ ዓለም አቀፍና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች እየተተገበሩ መሆናቸውን መከታተል፣ መወትወት እና አተገባበሩን በተመለከተ ግንዛቤን ማስፋት።

## የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች

የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችን ማለትም የመደራጀትና የመንቀሳቀስ ነጻነት፣ ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትና መረጃ የማግኘት መብት፣ በሕይወት የመኖር፣ የነጻነትና የደኅንነት መብት፣ የሕግ እኩል ጥበቃና ፍትሕ የማግኘት መብት፣ በፖለቲካና በመንግሥት አሠራሮች የመሳተፍ እና ከአድሎና ኢ-ሰብአዊ ከሆነ አያያዝ የመጠበቅ መብቶችን ማክበርና ማስከበር። በሲቪልና በፖለቲካ መብቶች ጥናትና ምርምር ማካሄድ። ምርመራ፣ ውትወታ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን።

## ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች

ለማኅበራዊ እና ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን መብቶች መከታተል እና ማስፋፋት። ዝቅተኛ ነገር ግን በቂ የሚባል የኑሮ ደረጃ እንዲኖራቸው የገቢ፣ የመጠለያ እና የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ይወተውታል። ባህሎቻቸውን እንዲያከብሩ፣ በቋንቋቸው የመናገር እና ሌሎች መብቶቻቸው እንዲጠበቁ የመንግሥት አካላትን መወትወት።

## የኢሰመኮ የ4 ዓመታት የለውጥ ጉዞ ስኬቶች

በመጋቢት ወር 2015 ዓ.ም. የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ባለሙያዎች ኮሚቴ ባደረገው 39ኛው መደበኛ ስብሰባ ለኮሚሽኑ የተባባሪ ደረጃን የሰጠ ሲሆን ይሄን ደረጃ ያገኘ 2ኛው የአፍሪካ የብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ሆኗል።

ሐምሌ 4 ቀን 2014 ዓ.ም. በተሻሻለው ዐዋጅ ቁጥር 1224/2012 መሠረት አንድ ምክትል ዋና ኮሚሽነር እና አንድ የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ መብቶች፣ የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች እንዲሁም የአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮሚሽነሮች ተሾሙ።


ጥቅምት 19 ቀን 2013 ዓ.ም. ዓለም አቀፍ የብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ጥምረት (The Global Alliance of National Human Rights Institutions (GANHRI)) ባደረገው ገለልተኛ ዓለም አቀፍ ምዘና ኮሚሽኑ የደረጃ “A” ዕውቅና (ወይም አንደኛ ደረጃ ዕውቅና “A” Status Accreditation) አገኘ።

የማቋቋሚያ ዐዋጅን ባሻሻለው ዐዋጅ ዐዋጅ ቁጥር 1224/2012 መሠረት ኢሰመኮ ተቋማዊ፣ የሰው ሀብት እና የፋይናንስ አስተዳደራዊ ነጻነት አገኘ።

የኮሚሽኑን ተልዕኮ መሸከም እና ውጤታማ አፈጻጸም ማስገኘት የሚያስችል አዲስ ድርጅታዊ መዋቅር እና የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ 2014 ዓ.ም. — 2018 ዓ.ም. ጸድቆ ተግባራዊ ተደረገ።

# የኢሰመኮ ተቋማዊ መዋቅር

ኮሚሽኑ በ2012 ዓ.ም. ከጀመራቸው የማሻሻያ ተግባራት ውስጥ አንዱ ተቋማዊ አደረጃጀቱን መገምገም እና በጥናት ውጤት ላይ የተመሠረተ የአደረጃጀት ማስተካከያ ማድረግ ነበር። በዚህም መሠረት ኮሚሽኑ ሕገ መንግሥታዊ ተልዕኮውን በውጤታማነት መፈጸም የሚያስችለውን ተቋማዊ አደረጃጀት ፈጥሯል። ከአደረጃጀቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሥራ ምዘና፣ የደመወዝ እና የጥቅማጥቅም ሥርዓት ቀርጾ እየተገበረ ይገኛል። የኮሚሽኑ አዲሱ እና በሥራ ላይ ያለው ተቋማዊ መዋቅር ከታች በሥዕላዊ መግለጫ የተገለጸውን ይመስላል።




*የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ተቋማዊ መዋቅር፣ 2012 ዓ.ም.*

# የኢሰመኮ የከተማ ቢሮዎች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) አዲስ አበባ ከሚገኘው ዋናው መሥሪያ ቤት በተጨማሪ በስምንት የክልል ከተሞች ጽሕፈት ቤቶች ያሉት ሲሆን እነርሱም በአሶሳ፣ በባሕር ዳር፣ በጋምቤላ፣ በሃዋሳ፣ በጅግጅጋ፣ በጅማ፣ በመቀሌ እና በሰመራ ይገኛሉ።




| ከተማ | Female | Male | ጠቅላላ የባለሙያ ብዛት |
|---|---|---|---|
| መቐለ | 0 | 3 | 3 |
| ሰመራ | 5 | 14 | 19 |
| ባሕር ዳር | 9 | 21 | 30 |
| አሶሳ | 3 | 16 | 19 |
| አዲስ አበባ | 105 | 68 | 173 |
| ጅግጅጋ | 8 | 12 | 20 |
| ጋምቤላ | 4 | 16 | 20 |
| ጅማ | 9 | 19 | 28 |
| ሃዋሳ | 8 | 19 | 27 |

## 3.1. የሰብአዊ መብቶች ትምህርት

ኢሰመኮ በሚከተሉት ተግባራት የሰብአዊ መብት ትምህርትን አሳድጓል፡፡

### የተከናወኑ ተግባራት

- የኮሚሽኑ ዋና ተልዕኮዎች ከሆኑት አንዱ የሆነውን የሰብአዊ መብቶች ስልጠናዎችን ለመሰጠት የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ በማካሄድ፣ የማሰልጠኛ መምሪያዎች በማዘጀትና ነባሮችንም በማሻሻል፣ በሪፖርት ዘመኑ በድምሩ 47 የስልጠና መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡፡ በእነዚህ ስልጠናዎች 909 ወንድ እና 430 ሴት ከባለግዴታ ተቋማት እና ከባለመብቶች የተውጣጡ በድምሩ 1339 ሰዎች ሰልጥነዋል፡፡ የስልጠና ውጤት ግምገማ ሥራዎችም ተከናውነዋል፡፡ ስልጠናዎቹ ከተለያዩ ክልሎችና ተቋማት ለተወጣጡ ሰልጣኞች በሚከተሉት ዐበይት ርዕሶች ዙሪያ ተሰጥተዋል፡-
    - በሰብአዊ መብቶች፣ ሰላም፣ አብሮነት እና መቻቻል፣
    - በሰብአዊ መብቶች እና የሽግግር ፍትሕ
    - በአካል ጉዳተኞች መብቶች፣
    - በሴቶችና በሕፃናት መብቶች፣
    - ከሕግ አስፈጻሚዎች ሥራ ጋር ተዛማጅ ስለሆኑ መብቶች፣
    - በተፈናቃዮች እና ስደተኞች መብቶች፣
    - የሰብአዊ መብቶች ከዘላቂ የልማት ግቦች ጋር ያለው ትስስር፣
    - የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች የሰብአዊ መብቶችን በማስፋፋት ስላላቸው ሚና፣ ወዘተ...

- ለእያንዳንዱ ስልጠና ባለመብቶችን እና ባለግዴታዎችን ማእከል ያደረጉ የማሰልጠኛ መምሪያዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ መመሪያዎቹ የተቀረጹት እና የቀረቡት ተሳታፊዎች መብቶቻቸውን እንዲያውቁ እና እንዲጠቀሙባቸው ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ስለሰብአዊ መብቶች ያላቸውን ዕውቀት በብቃት ለሌሎች ለማካፈል ክህሎት እንዲኖራቸው በማድረግ ሰብአዊ መብቶችን እንዲያስፋፉ ተጽዕኖ ለመፍጠር ነው፡፡

- ከዚህም በተጨማሪ ኮሚሽኑ ሰብአዊ መብቶችን በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ለማሥረጽ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ የመሥራት ተግባራትን አከናውኗል፡፡

- በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሰብአዊ መብቶች ዕውቀትን ለማዳበር ሦስተኛውን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሰብአዊ መብቶች የምስለ ችሎት (moot court) ውድድር አካሂዷል፡፡

- ሰብአዊ መብቶችን ለማስፋፋት እና ለማስተማር ኮሚሽኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚሠራ ሲሆን የኪነጥበብ አማካሪ ቡድን አቋቁሞ በትብብር እየሠራ ቆይቷል፡፡ የትብብሩ ዓላማ ኪነጥበብን ያለውን ኃይል በመጠቀም ሰብአዊ መብቶችን ለማስተዋወቅ ነው፡፡

- የሰብአዊ መብቶች ትምህርት የሥራ ክፍል ባልደረቦች ከነሐሴ 30 እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ ወደ ጋና በመጓዝ ከጋናው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም- Commission on Human Rights and Administrative Justice (CHRAJ) ጋር የ5 ቀናት የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡

- የሥራ ክፍሉን ባለሙያዎች የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን ዕውቀት ለመገንባት የሚረዳ የበይነ መረብ ስልጠና በዘርፉ ታዋቂ በሆኑ ባለሞያ እና በሰብአዊ መብቶች ትምህርት ባለሞያዎች ማኅበር በኩል ከመጋቢት 27 ቀን እስከ ግንቦት 8 ቀን 2015 ዓ.ም. እንዲወስዱ ተደርጓል። ስልጠናው በስርዓተ ትምህርት ቀረጻ፣ የስልጠና አሰጣጥ እና የግምገማ ዘዴዎች ክህሎታቸውን ማሳደግ ላይ ያተኮረ ነበር።

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- በእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በተሰጡ ስልጠናዎች ተሳታፊዎች በየበኩላቸው የሰብአዊ መብቶችን ተረድተው እንዲያከብሩ እና እንዲያስከብሩ አግዟቸዋል። ለሌሎች የማስረዳት ዐቅማቸው እንዲዳብር አስችሏል። በየዘርፉ ባሉ የሰብአዊ መብቶችን በማስፋፋት ተግባራት ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማብቃት ተችሏል።
- የባለመብቶች ማኅበራትንና እና የአባላቶቻቸውን የሰብአዊ መብቶች ዕውቀትና ክህሎት መገንባት ተችሏል።
- የወንጀል ተጠርጣሪዎች እና ተከሳሾች ፣ ሴቶች እና ሕፃናት፣ ተፈናቃዮች እና ስደተኞች መብቶችን ለማስጠበቅ የሚያስችል የመብት ባለግዴታዎችን ዕውቀት፣ ክህሎት እና ባህሪን አሻሽሏል።
- የተማሪዎችን የሰብአዊ መብቶች ዕውቀትና ክህሎት ለማዳበርና ለማሳደግ የሚያስችል የትምህርት ሥርዓት ለመዘርጋት ያለመ ግንኙነት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ተፈጥሯል።

## 3.2. የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ

የኮሚሽኑ መሠረታዊ ተልዕኮ የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ ማድረግ ሲሆን በዚህ መስክ በሪፖርት ዘመኑ ውጤታማነት የተመዘገበበት ነበር።

### የተከናወኑ ተግባራት

#### ክትትልና ምርመራ ሥራ

- በሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ ሥራ መስክ የሚከተሉት ዐበይት ተግባራት ተከናውነዋል፡-
  - የማረሚያ ቤቶች እና የፖሊስ ጣቢያዎች ክትትል በተመለከተ በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 89 ማረሚያ ቤቶችን፣ 447 ፖሊስ ጣቢያዎች እና ይፋዊ ያልሆኑ የተጠርጣሪ ማቆያዎችን ለመጎብኘት ታቅዶ 64 ማረሚያ ቤቶች (71.9%) እና 377 ፖሊስ ጣቢያዎች (84.3%) ላይ በተጨማሪም 16 ይፋዊ ያልሆኑ የተጠርጣሪ ማቆያዎች ክትትል ተደርጓል።
  - በተጨማሪ ከተያዙ ሰዎች አያያዝና መሠረታዊ አቅርቦቶች፣ ከታራሚዎች ጋር በተያያዘ የተስተዋሉ ጉድለቶች መታረም እንዲችሉ 30 የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት በክልል እና ፌዴራል ደረጃ የሚገኙ የበላይ ሥራ ኃላፊዎች፣ የሕዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤት አባላት እና ሌሎች የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በጋራ በክትትል ግኝቶች እና በምክረ ሐሳቦች ላይ ውይይት/ ምክክር አካሂደዋል።

| ክትትልና ምርመራ ሥራ | |
|---|---|
| ማረሚያ ቤቶች | 64 |
| ፖሊስ ጣቢያዎች | 377 |
| ይፋዊ ያልሆኑ የተጠርጣሪ ማቆያዎች | 16 |

#### የመብት ጥሰት አቤቱታዎች ቅበላ እና መስተንግዶ

- በአጠቃላይ በ2123 አቤቱታዎች (በአካል በመቅረብ፣ በ7307 ነፃ የስልክ መስመር እና በኢሜል) በአዲስ አበባ መሥሪያ ቤት 504፣ በከተማ ጽሕፈት ቤቶች 1619 (አሶሳ 77፣ ባሕር ዳረ 266፣ ጋምቤላ 53፣ ሃዋሳ 282 ጂግጂጋ 46፣ ጂማ 833 እና ሰመራ 62) ተቀብሎ አስተናግዷል። ከአጠቃላይ አቤቱታ ካቀረቡ ሰዎች መካከል 76.1% ወንዶች ሲሆኑ የተቀሩት ሴቶች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 141 የሚሆኑት አቤቱታ አቅራቢዎች አካል ጉዳተኞች ናቸው። ከተስተናገዱት ጉዳዮች መካከል 1406 ወይም 66.2% ተቀባይነት ያገኙ ሲሆን የተቀሩት ጉዳዮች (35.8%) በኮሚሽኑ ሥልጣን ሥር ስለማይወድቁ በምክር ተዘግተዋል። ተቀባይነት አግኝተው ከተስተናገዱት 1406 ጉዳዮች መካከል 851 ጉዳዮች (60.5%) መፍትሔ እንዲያገኙ ተደርጓል።

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የቀረበ አቤቱታ | 2123 |
| ተቀባይነት ያገኙ አቤቱታዎች | 1406 |
| ተቀባይነት ያላገኙ አቤቱታዎች | 717 |
| መፍትሔ ያገኙ አቤቱታዎች | 851 |
| መፍትሔ ያላገኙ አቤቱታዎች | 555 |

**የቀረቡ አቤቱታዎች በከተማ ጽሕፈት ቤቶች**

| | |
|---|---|
| አዲስ አበባ መሥሪያ ቤት | 504 |
| ጅማ ጽ/ቤት | 833 |
| ባሕር ዳር ጽ/ቤት | 266 |
| ሃዋሳ ጽ/ቤት | 282 |
| ጋምቤላ ጽ/ቤት | 53 |
| ሰመራ ጽ/ቤት | 62 |
| ጅግጅጋ ጽ/ቤት | 46 |
| አሶሳ ጽ/ቤት | 77 |
| ጠቅላላ | 2123 |

## አቤቱታ የቀረበባቸው ጉዳዮች፣ ተቋማት እና የመብት ጥሰቶች

- የመብት ጉዳዮች አብዛኞቹ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች (53%) የተቀሩት ጉዳዮች ደግሞ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች እንዲሁም ሌሎች የቡድን መብቶች ይገኙበታል::
- አቤቱታ ከቀረበባቸው የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች መካከል በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎች መብቶች ጥሰቶች በዋናነት ይጠቀሳል::
    - ሕገ ወጥ እ ሥራት፣
    - ፍርድ ቤት ያለመቅረብ፣
    - ጉብኝት መከልከል፣
    - የዋስትና ትእዛዞች ያለመከበር፣
    - ማሠቃየትና ኢ-ሰብአዊ አያያዝ ወዘተ እና
    - መድልዎ ሲሆኑ መድልዎን የሚመለከቱት ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ::
- አቤቱታ ከቀረበባቸው ተቋማት መካከል ከፍተኛ ቁጥር የሚይዙት የሕግ አስከባሪ አካላት ሲሆኑ በተለይም የክልል እና ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽኖች እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ዋናዎቹ ናቸው::
- የኮሚሽኑ የክትትልና ምርመራ ሥራዎች በተሟላ መልኩ በመረጃ ላይ የተመረኮዙ እንዲሆኑ ለማድረግ ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ የጉዳዮች ፍሰት መምሪያ ሥርዓት (Electronic Case Management System) ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል:: በሪፖርት ዘመኑ ዋናው መሥሪያ ቤትን ጨምሮ ለአራት ጽ/ቤቶች የቀረቡ አቤቱታዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ሲስተሙ እንዲገቡ ለማድረግ ተችሏል::
- ኮሚሽኑ የክትትል እና ምርመራ ሥራ በወጥ የአሠራር ሥርዓቶች እና መመሪያዎች የታገዘ ለማድረግ የክትትል እና የተንቀሳቃሽ የሰብአዊ መብቶች አቤቱታ ማስተናገጃ የሥራ መምሪያዎች ተዘጋጅተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል::
- ከሁሉም ጽ/ቤቶች ለተወጣጡ 30 ባለሙያዎች የdigital investigation and online research techniques እና ለ22 ባለሙያዎች በምርምርና ክትትል፣ ፈጣን ምላሽ፣ የሪፖርት ዝግጅትና የሰብአዊ መበቶች ውትወታ ላይ ስልጠናዎች ተሰጥቷል::

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

በማረሚያ ቤቶችና በፖሊስ ጣቢያዎች በተደረገ ክትትል እና በምክረ ሐሳቦች ተፈጻሚነት ላይ በተደረገ ውትወታ እና የጋራ ውይይት፡-

- በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ለታራሚዎች የተመደበው የምግብ በጀት ከ22 ብር ወደ 35 ብር ከፍ ተደርጓል፡፡
- የማረሚያ ቤቶች ምድረ ጊቢዎች፣ መኝታ ክፍሎች እና ንጽሕና መጠበቂያ ክፍሎች ንጽሕናቸው ተሻሽሏል፡፡ የተበላሹ የሕዝብ ስልኮች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡
- በፌዴራል የሕምክና ተቋማት ተቋርጦ የነበረው የታራሚዎች ሕክምና አገልግሎት እንደገና እንዲጀምር ተደርጓል፡፡
- ከእናቶቻቸው ጋር በማረሚያ ቤት የሚገኙ ሕፃናት አማራጭ የእንክብካቤ አገልግሎት እንዲያገኙ ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ስምምነት ተፈርሟል፡፡ ከከተማ አስተዳደሩ ሴቶችና ሕፃናት ቢሮ ጋር በተደረገ ውይይት ሕፃናቶቹ በማረሚያ ቤት እንዳሉ በተመላላሽ አልያም በሕፃናት ማቆያ ሆነው ትምህርታቸውን ሊከታተሉ የሚችሉበት አማራጭ እያፈላለገ ይገኛል፡፡
- የበርካታ ሲቪል ሰዎችን ሞት፣ አካል ጉዳት እና ንብረት ውድመት ያደረሱ የመብት ጥሰቶች እውነታቸው እንዲታወቅ እና መንግሥት ለሚወስዳቸው የተጠያቂነት እና የመፍትሔ እርምጃዎች መነሻ ሆነዋል፡፡
- ፍ/ቤት በወቅቱ መቅረብ የሚገባቸው ሰዎች እንዲቀርቡ፣ ድብደባ እንዲቆም፣በርካታ ከሕግ አግባብ ውጪ የታሰሩ ሰዎች ከእስር እንዲፈቱ፣ የዋስትና የፍርድ ቤት ውሳኔዎች እንዲከበሩ፣ በእስር ላይ የሚገኙ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሕክምና እንዲያገኙ ወዘተ... በማድረግ ረገድ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል፡፡

## 3.3. የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች

### የተከናወኑ ተግባራት

- የሕፃናት በቂ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብትን የሚመለከቱ በሕግ ማዕቀፎች ረገድ ያሉ ክፍተቶች ተለይተው ምክረ ሐሳቦች ለባለድርሻ አካላት ቀርበዋል፡፡
- የአማራ ክልል የሴቶች የገጠር መሬት መብትን በተመከለተ በሕግ ማዕቀፎች ረገድ ያሉ ክፍተቶች ተለይተዋል፡፡
- በጎዳና ላይ ያሉ ሕፃናት መብቶች ሁኔታን በተመለከተ ክትትል ተደርጓል፡፡ የመብት ጥሰቶች ተለይተው ምክረ ሐሳቦች ቀርበዋል፡፡
- በሶማሊ ክልል በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የሚያልፉ ሕፃናትን ሰብአዊ መብቶች ሚመለከቱ ችግሮች ተለይተው ምክረ-ሐሳቦች ለባለድርሻ አካላት ቀርበዋል፡፡
- በአዲስ አበባ በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ውስጥ ያሉ ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ተደርጎ በዚህ ረገድ ያሉ ችግሮች ተለይተው ምክረ ሐሳቦች ለባለድርሻ አካላት ቀርበዋል፡፡
- በአማራ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ፤ ኦሮሚያ፣ አፋር ክልሎችና አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሴቶችና በሕፃናት መነገድ የተሰጠው ሀገራዊ ምላሽ ከሰብአዊ መብቶች አንጻር ተገምግሞ ያሉ ተግዳሮቶች ተለይተዋል፤ ምክረ-ሐሳቦች ለባለድርሻ አካላት ቀርበዋል፡፡
- የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ጥሰቶች፣ የሕግ፣ የፖሊሲ እና የአሠራር ክፍተቶች ተዳሰዋል፡፡ የተዳሰሱ ዋና ዋና አሳሳቢ ጉዳዮችን ለባለግዴታዎች በማስገንዘብ የምክረ ሐሳቦቹን ተፈጻሚነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል በኮሚሽኑ ዋና ጽ/ቤት እና በከተማ ጽ/ቤቶች ከሚገኙ ባለግዴታዎች ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡

### የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- በአማራ፣ በሐረሪ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ እና በደቡብ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ የሕፃናት መንከባከቢያና ማሳደጊያ ተቋማት ውስጥ ያሉ ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ከአዲስ አበባ ከተማ፣ ደቡብ ክልል ስልጤና ጉራጌ ዞን፣ ከኦሮሚያ እና ከሲዳማ ክልሎች ለተውጣጡ ሴቶች እና ሕፃናት መብቶች ላይ ለሚሠሩ ማኅበራት እና ተቋማት አባላት እና ባለሙያዎች የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ዳብሯል፡፡
- በሃዋሳ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ወረዳዎች በሴቶች እና ሕፃናት ላይ ስለሚከሰቱ የጠለፋ ድርጊቶች መጠን እና ስፋት ደረጃ ለማመላከት እና ውትወታ ለማድረግ የሚያስችሉ ግብዓቶችን ለማግኘት ተችሏል፡፡

## 3.4. አከል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች





### የተከናወኑ ተግባራት

- በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና በ7 ክልሎች የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እና ዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤቶች ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ያላቸው ተደራሽነትን በተመለከተ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ተከናውኗል፤ ከባልደርሻ አካላት ጋር ምክከር ተደርጓል።

- አካል ጉዳተኞች ከቀረጥ ነጻ የሚያስገቧቸው ተሽከርካሪዎች ላይ ልዩ ሰሌዳ ለመለጠፍ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የወጣውን መመሪያ ለማስተግበር የተላለፈውን ውሳኔ አስመልክቶ የመመሪያው መተግበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ላይ ሊያሳድር በሚችለው ተፅዕኖ ዙሪያ ክትትል ተካሂዷል። አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በተለያየ ደረጃ የውትወታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

- በ2014 ዓ.ም. በአፋር እና አማራ ክልሎች በግጭቱ ወቅትና ከግጭቱ በኋላ የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ ላይ ክትትል ተካሂዷል። በግኙቱ መሠረት ተዘግቶ የቆየውና በአፋር ክልል የሚገኘው የአካል ጉዳተኞች የተኃድሶ ማእከል ተመልሶ ወደ ሥራ ሊገባ የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ኮሚሽኑ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር የውትወታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ይህም ከግጭቱ በፊት የአካል ጉዳት ለነበረባቸው እና በግጭቱ ምክንያት ለአካል ጉዳት ለተዳረጉ ሰዎች ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎችንና ከመልሶ ማገገም ጋር የተገናኙ አገልግሎቶችን በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ያስችላል።

- በአጣዬ፣ ደብረ ብርሃን፣ ሃዋሳ፣ በመቂ እና ሻሸመኔ ከተሞች በሚገኙ የአረጋውያን መንከባከቢያ ማእከላት የአረጋውያን መብቶች መከበራቸውን የክትትል ሥራ ተከናውኗል። የክትትል ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት እና ለሕዝብ ይፋ ተደርጓል።

- ለከፍተኛ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም ለሲቪክ ማኅበራት ስለ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲጨብጡ እና የተ.መ.ድ. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት መከበር ዙሪያ ዐቅማቸው እንዲጎለብት ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። ኮሚሽኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የሚተገብራቸው ሥራዎች የበለጠ ውጤታማ እና ተደራሽ እንዲሆኑ አድርጓል።

- አረጋውያንን እና አካል ጉዳተኞችን የተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሑፎች እና የድምጸ-ምስል

ውጤቶች በኮሚሽኑ ድረገጽና በሌሎች መገናኛ ብዙኃን እንዲ ሠራጭ ተደርጓል፡፡

- በአካል ጉዳተኞች የሥራ መብት ዙሪያ ለኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የአቻ ግምገማ ላይ በተሰጠ ምክረ ሐሳብ ላይ ትምህርት ሰጪ



መልእክት፤

- ስለ ሴሬብራል ፓልዚ፣ኤፐለፕሲ፣ የአእምሮ እድገት ውስንንት፣ ዳውን ሲንድሮም፣ ኦቲዝም እና ሰብአዊ መብቶች በሚል ርዕስ የተዘጋጁ መረጃ ሰጪ ጽሑፎችና የድምጸ ምስል ውጤቶች፤
- የአረጋውያንን ሰብአዊ መብቶች ለመጠበቅ እና ለማስፋፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ የአረጋውያን መብቶች ስምምነት አስፈላጊነት በሚል ርዕስ የባለሙያ አስተያየት፤
- በሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ እና ተካታችነት በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ትምህርታዊ ጽሑፍ፤
- ኮሚሽኑ በአካል ጉዳተኞች የአካል ጉዳተኝነት ዕይታዎች (disability models) ላይ ያተኮረ አጭር የተንቀሳቃሽ ምስል ቪድዮ በትግርኛ፣ አፋን ኦሮሞ እና ሶማሊኛ የተዘጋጀ፤

- ከሀጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ጋር ትስስር ለመፍጠር በተደረገው እንቅስቃሴ፡-
  - በጋምቢያ ባንጁል ከተማ በተካሄደው 73ኛው የአፍሪካ ኮሚሽን መደበኛ ጉባኤ ላይ የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋውያንን ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ የሚያሳይ ጽሑፍ ቀርቧል፡፡
  - በደቡብ አፍሪካ ከደቡብ አፍሪካ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና ከሌሎች ሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና ከአውስትራሊያ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር የሥራ ልምድ



ልውውጥ ተካሂዷል፡፡

  - በዓለም አቀፍ የብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ትብበር (The Global Alliance of National Human Rights Institutions (GANHRI)) የአረጋውያን ሰብአዊ መብቶች የሥራ ቡድን (Working Group on Aging and the Human Rights of Older Persons) ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ሰብአዊ መብቶች ኮንቬንሽን ረቂቅ ዙሪያ ለመወያየት በደቡብ ኮርያ ሪፐብሊክ ሴኡል ከተማ በተካሄደ ስብሰባ ላይ ኮሚሽኑ ተሳትፏል፡፡ ስብሰባውን ተከትሎ በተካሄደው ኮንፍረንስ ላይ ኮሚሽኑ 'Family and Community Care and Protection for Older Persons.' በሚል ርዕስ ጽሑፍ አቅርቧል፡፡

- ○ በተመድ የሚገኘው ገለልተኛ ኤክስፐርት (Independent Expert) በጠየቀው መሠረት በአረጋውያን የሚደርስ የመብት ረገጣ፣ ጥቃት እና መረሳት (መተው) (violence, abuse, and neglect against Older Persons) ላይ ጽሑፍ አስገብቷል፡፡

- ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ትብብርና አጋርነት ለመፍጠር የሚያስችሉ ከባለድርሻ፣ ከአጋር አካላት፣ ከኪነጥበብ እና ከመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ጋር የምክክርና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተካሂደዋል፡፡

- በሀገር አቀፍ ደረጃ የአካቶ ትምህርት ፖሊሲ እና የአሠራር ለውጥ ለማምጣት ውትወታ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ በአዲስ አበባ፣ በጎንደር፣ በሐረማያ፣ በጅማ እና ሃዋሳ ዩንቨርሲቲዎች ላይ የአካል ጉዳተኞችን የከፍተኛ ትምህርት ተካታችነት በተመለከተ የሰብአዊ መብቶች ክትትል አካሂዷል፡፡

- የአሠራርና ሠራተኞችን ዐቅም ለመገንባት የሥራ ክፍሉ ያደራጃቸው የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች መብቶች አምባሳደሮች ቡድን አባላት በሥራ ክፍሎቻቸው ውስጥ የሠሯቸውን ሥራዎች እና ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች በመሰብሰብ ዘገባ እና አካል ጉዳተኞችን የማካተት መመሪያ (Disability Mainstreaming Guideline) በማዘጋጀት ከአምባሳደሮቹ ጋር በመወያየት ለቀጣይ ሥራዎች የድርጊት ነጥቦችን ለይቷል፡፡ የሥራ ክፍሉ አምባሳደሮቹ በመመሪያው መሠረት የማካተት ሥራውን ማከናወናቸውን እና ያጋጠሟቸው ተግዳሮቶች አስመልክቶ ክትትል አድርጓል፡፡

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- ከባለድርሻ አካላት ጋር በተካሄዱ የውይይት መድረኮች በክትትል ግኝቶችና ሊተገበሩ በሚችሉ ምክረ ሐሳቦች ላይ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

- በአካል ጉዳተኞች እና በአረጋውያንን መብቶች ዙሪያ በተሰጡ ስልጠናዎች፣ በመገናኛ ብዙኃን እና በሌሎች መንገዶች በሚ ሠራጩ መልእክቶች የባለመብቶች፣ የባለግዴታዎች፣ የባለሙያዎችና ሌሎች የባለድርሻ አካላት ግንዛቤን ማዳበር ተችሏል፡፡

- ኮሚሽኑ በሰጠው ምክረ ሐሳብ መሠረት የአረጋውያን መንከባከቢያ ማእከላቱ የአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል አሳይተዋል፡፡

- ሠራተኞች በወሰዱት የዐቅም ግንባት ስልጠና ምክንያት በክትትል ሥራ እና በሪፖርት አጻጻፍ ዘዴ ላይ ያላቸው ዕውቀት ዳብሯል፤ በተግባር መሻሻል ታይቷል፡፡

## 3.5. የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና የፍልሰተኞች መብቶች

### የተከናወኑ ተግባራት

- **የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በተመለከተ:**
  - ብሔራዊ የካምፓላ ስምምነትን ማስፈጸሚያ ሕግ እንዲወጣ ኮሚሽኑ ከዚህ ቀደም ሲያደርግ የቆየውን የውትወታ ሥራ በማጠናከር 'የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃና ድጋፍ' ረቂቅ ዐዋጅ ዝግጅት ላይ ትልቅ የሚባል አስተዋጾዖ አድርጓል፡፡
  - ከደቡብ ምዕራብ ክልል ከፋ ዞን ዴቻ ወረዳ እና በከምባታ ጠምባሮ ዞን ዶዮ ገና ወረዳ በ2011 ዓ.ም ተፈናቅለው ወደ ቀያቸው መመለስ ያልቻሉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በሚመለከት በተካሄደው ምርመራ የተለዩ አንኳር ጉዳዮች እና የተሰጡ ምክረ-ሐሳቦች ዙሪያ በሚዛን ከተማ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ተካሂዷል፡፡
  - በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ከመኖሪያ ቀያቸው በመፈናቀላቸው በሰሜን ጎንደር ዞን ዳባት ወረዳ ሽመላኩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያ ጣብያ፣ ዳባት ከተማ እና በወረዳው የተለያዩ ቀበሌዎች ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ተፈናቃዮችን እና ወደ አዲአርቃይ ወረዳ እንዲመለሱ የተደረጉ ተመላሾችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እና የሰብአዊ ድጋፍ አቅርቦት እና ተደራሽነት በተመለከተ ክትትል ተደርጓል፡፡
  - በአፋር፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያ፣ በሶማሊ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ከ 369,000 በላይ የሚሆኑ ተፈናቃዮችና ተመላሾችን የሚያስጠልሉ 52 መጠለያ ቦታዎች፣ ጣቢያዎች እና ተቀባይ ማኅበረሰቦች ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡
  - በደቡብ ክልል በአምስት ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች ከጥር 28 እስከ 29 ቀን 2015 ዓ.ም. በተካሄደው የሕዝበ ውሳኔ ላይ ለተፈናቃይ መራጮች በተሰናዱ በ07 ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች እና ተፈናቃዮችም ተመዝግበው በመረጡባቸው 4 መደበኛ ጣቢያዎች ላይ በመገኘት የቅድመ ሕዝበ ውሳኔና የሕዝበ ውሳኔው ቀን ክትትል ተከናውኗል፡፡

- **ፍልሰተኞችን በተመለከተ**
  - መደበኛ ባልሆነ ስደት ላይ የ ሕግ ማዕቀፎች እና የአፈፃፀም ሁኔታን በተመለከተ ግምገማ ተካሂዷል፡፡
  - በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን፣ በሃዲያ ዞን፣ በጋሞ ዞን እንዲሁም በወላይታ ዞን በሚገኙ 12 ወረዳዎች ውስጥ ያለውን የሕፃናት ፍልሰተኞች መብቶች አያያዝ ክትትል ተደርጓል፡፡ በተለዩ ግኝቶችና በተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡

- **ስደተኞችን በተመለከተ**
  - በአዲስ አበባ ከተማ ለእስር የተዳረጉ የኤርትራዊያን ስደተኞችን በተመለከተ በፖሊስ መምሪያዎች ላይ የክትትል ተደርጓል እንዲሁም የኤርትራዊያን ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች እስርን እና በኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ኤርትራ እንዲመለሱ የተደረገበትን አግባብ በሚመለከት መግለጫ ወጥቷል፡፡
  - በጋምቤላ እና በአማራ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ከ72,100 በላይ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚገኙባቸውን 20 የስደተኞች መጠለያዎች እና መቀበያ ማዕከላት ላይ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክትትል ተደርጓል፡፡

- የተፈናቃዮች፣ የስደተኞች እንዲሁም የፍልሰተኞች መብቶች አጠባበቅና አተገባበር

ሁኔታ እንዲሻሻል መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ የሲቪክ ማኅበራት እና ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ተቋማት ጋር ትስስርና አጋርነት ተፈጥሯል።

የተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶቻቸውን በማስከበር ሂደት የተጠናከረ ሚና እንዲኖራቸው የውትወታ ሥራ ተሠርቷል።

- በተፈናቃዮች እና በስደተኞች ሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ዙሪያ ለባለግዴታዎችና አገልግሎት ሰጪዎች ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። እንዲሁም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ግንዛቤ የማስጨብጥ ሥራዎች ተሠርተዋል።
- በተጨማሪ ከUNHCR እና ከGIZ ጋር እ.ኤ.አ. በ2023 በሚከናወኑ ሥራዎች፣ የሥራ ክፍሉን ዐቅም ማጎልበት እና የጋራ ሥረዎች በማከናወን ዙሪያ የመግባቢያ ሰነዶች ታድሰዋል።
- ለአፍሪካ ሕዝቦች እና የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ACHPR) የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን እና ፍልሰተኞች መብቶች ሁኔታን የተመለከቱ ሪፖርት ተጠናቅሮ ተልኳል።
- ከዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት (ILO) እና ከዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት (IOM) ጋር በመተባበር በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፍትሕ ሚኒስቴር ሥር ለተቋቋመው ብሔራዊ የትብብር ጥምረት ኢሰመኮን ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ግብአት ስጥቷል።

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- የተከናወኑት ጥናቶችና ዳሰሳዎች ያሉትን የሕግና የትግበራ ክፍተቶች አሳይተዋል፤ ኮሚሽኑ በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት መጠቆም ተችሏል።
- የተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶችን በበቂ ሁኔታ ያካተተ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃና ድጋፍ ረቂቅ ዐዋጅ ተዘጋጅቷል።
- የተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች አጠባበቅ፣ የተስተዋሉ አንኳር ችግሮች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች እና እርምጃዎችን በተመለከተ የሚመለከታቸው አካላት መረጃ አግኝተዋል እንዲሁም ግንዛቤያቸው ዳብሯል።
- አጋርነት በመመሥረት እና የቅብብሎሽ ሥርዓት ውስጥ ካሉ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥን በማመቻቸት ባለመብቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።
- ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ሥራዎች ተለይተዋል። በዚህም መሠረት የጋራ ሥራዎች ተጀምረዋል፤ ለባለመብቶች በሚደረግ ድጋፍ ላይ የተሻለ ውጤትና ተደራሽነት ሊኖር ችሏል።

## 3.6. የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች

### የተከናወኑ ተግባራት

- በሪፖርት ዘመኑ አራት በሕዝብ ፊት የሚካሄዱ ብሔራዊ/ ግልጽ ምርመራዎች (National Inquiry/Public Inquiry) ነጻነታቸውን ከሕግ ውጪ እና በዘፈቀደ በተነፈጉ ሰዎች ላይ በማተኮር በአዳማ፣ ባሕር ዳር፣ በጅግጅጋና በሃዋሳ፣ ከተሞች ተካሂደዋል። በዚህም ነጻነታቸውን ከሕግ ውጪ እና በዘፈቀደ በተነፈጉ ሰዎች ላይ የደረሰን ስልታዊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በመለየት የሚመለከታቸው አካላት እንዲመክሩባቸው ተደርጓል።

- ከአማራ ክልል የፖሊስ ኮሚሽን፣ ሰላም እና ጸጥታ አስተዳደር፣ የምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ፣ ዋና ኦዲተር፣ የሰላም፣ ፍትሕ እና ዴሞክራሲ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ፍትሕ ቢሮ እና ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት በተገኙበት በተመረጡ የመብት ጥሰቶች ላይ የምርመራ እና ክትትል ሪፖርት ግኝቶች እና በቀረቡ ምክረ ሐሳቦች ላይ ምክክር ተደርጓል።

- ከምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የ6ተኛው ብሔራዊ አጠቃላይ ምርጫ ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ረቂቅ ሪፖርትን በተመለከተ ሁለት የምክክር መድረኮች በማዘጋጀት ግብአት ተገኝቷል።

- የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ተጎጂዎች ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል የተጎጂዎች ማካካሻ ፈንድ ለማቋቋም የሚያስችል ረቂቅ የፖሊሲ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

- የቅድመ ክስ እስረኞች ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመገምገም የሚረዳ መነሻ ጽሑፍ፣ የሕግ ትንተና እና መረጃውን ለመሰብሰብ የሚረዳ የክትትል መሣሪያ ተዘጋጅቷል። እንዲሁም የቅድመ ክስ እስረኞችን በተመለከተ ከአማራ፣ ደቡብ፣ አዲስ አበባ እና ኦሮሚያ ክልሎች መረጃ ተሰብስበዋል።

- በመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም ዙሪያ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ላይ ጥናት ተካሂዶ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

- በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች እና የዘላቂ ልማት ግቦች አተገባበር ላይ ያተኮረ የግምገማና የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የተሰጡ ምክረ ሐሳቦችን ያካተተ ረቂቅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

- በቀድሞው ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም. በተካሄደው ሕዝበ ውሳኔ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክትትል በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች ተከናውኗል።በተጨማሪም ሁለት ዙር በተመረጡ ዞኖች እና ወረዳዎች ቅድመ ሕዝበ ውሳኔ ክትትል ተካሂዷል፤ ረቂቅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

- በረቂቅ ደረጃ ላይ ያሉ ሕጎችን ከሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ጋር ተስማሚ መሆናቸውን በመገምገም ለሚመለከተው አካል አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

- በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች አያያዝ ላይ የሚያተኩር ዓመታዊ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

- ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታዩ ያሉ የሚዲያ ባለሙያዎችን፤ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትንና ደጋፊዎች እንዲሁም የሲቪል ማኅበራት የፍርድ ሂደት ላይ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች አጠባበቅ ሁኔታን

ለመከታተል የሚረዳ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን ለማሻሻል በተዘጋጀው ረቂቅ ዐዋጅ ላይ ከሲቪልና ፖለቲካ መብቶች አንጻር በጽሑፍና እንዲሁም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተዘጋጀው የውይይት መድረክ በመገኘት ተጨማሪ ግብዓት ተሰጥቷል፡፡

- በአፍሪካ ውስጥ በመያዝ ወቅት፣ በፖሊስ ጥበቃ ሥር በማቆየት እና በቅድመ-ክስ እስር የማቆያ ቦታዎች ስለሚኖረው የአያያዝ ሁኔታ መመሪያ በአማርኛ ተተርጉሞ ታትሟል፡፡

- በዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ሁሉን አቀፍ የአቻ ግምገማ (Universal Periodic Review) እና የማሰቃየት፣ የጭካኔ እና ኢሰብአዊ አያያዝን እና የእ ሥራት ሁኔታዎችን የሚመለከቱ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ እና በዓለም አቀፍ የአቻ ግምገማ ለኢትዮጵያ የተሰጡ ምክረ-ሐሳቦች በሬዲዮ በማ ሠራጨት በጉዳዩ ዙሪያ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳድግ ሥራ ተናውኗል፡፡

- ለተ.መ.ድ. ጭካኔ እና ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ኮሚቴ (Committee on Torture/CAT) የኢትዮጵያ መንግሥት ለኮሚቴ ያቀረበውን ሪፖርት መሠረት በማድረግ እና ትኩረት በተሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ሪፖርት በማዘጋጀት ለኮሚቴው ተልኳል፡፡

- በኢትዮጵያ ከሚያዝያ 2014 ዓ.ም. እስከ መስከረም 2015 ዓ.ም. እና ከመስከረም 2015 - ሚያዝያ 2015 ዓ.ም. ድረስ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች አያያዝ ሁኔታን የሚመለከቱ ሁለት ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ተልኳል፡፡

- ከOffice of the United Nations High Commissioner for Human Rights በመተባበር ሰባት አጠቃላይ ትንታኔ (General Comments) በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው እየተሠራጩ ይገኛሉ፡፡ እነርሱም፦
    - አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 21፦ አንቀጽ 10 በነጻነት የመንቀሳቀስ መብታቸውን የተነፈጉ ግለሰቦችን በሰብአዊነት ስለመያዝ፣
    - አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 27፦ አንቀጽ 12 የመንቀሳቀስ መብት፣
    - አጠቅላይ ትንታኔ ቁጥር 32፦ አንቀጽ 14 በፍርድ ቤቶች እና በችሎቶች ፊት በእኩልነት የመዳኘት እና ፍትሐዊ ዳኝነት የማግኘት መብት፣
    - አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 35፦ አንቀጽ 9 የግለሰብ ነጻነትና አካላዊ ጥበቃ፣
    - አጠቅላይ ትንታኔ ቁጥር 34፦ አንቀጽ 19 ሐሳብን በነጻነት የመያዝና የመግለጽ መብት፣
    - አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 20፦ አንቀጽ 7 ከማሠቃየት እና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዞችና ቅጣቶች መጠበቅ፣ እና
    - አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 36፦ አንቀጽ 6 በሕይወት የመኖር መብት ናቸው፡፡

- የሠራተኞችን ዐቅም ለመገንባት በዘጠኝ ወራት ውስጥ በሥራ ክፍሉ የተከናወኑ ተግባራትን ከሌሎች የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን በደቡብ አፍሪካ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በመገኘት የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡

- አጋር ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት በሚያዘጋጇቸው የሙያ፣ የክህሎትና የዕውቀት ግንባታ ስልጠናዎች/ውይይቶች ላይ ተሳትፎ በማድረግ የሥራ ክፍሉ ባለሙያዎች ዐቅማቸውን እንዲገነቡ ተደርጓል፡፡

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች



## 3.7. ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች

### የተከናወኑ ተግባራት

- በፌዴራልና በክልል መንግሥታት የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶችን አስመልክቶ የወጡና ተፈጻሚ እየሆኑ የሚገኙ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ዳሰሳ እና የኢኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ልየታ ረቂቅ ጥናት ተጠናቋል።

- በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን እና በሶማሊ ፋፈን ሸበሌ እና ጀረር ዞኖች የተከሰተውን ድርቅ አስመልክቶ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ሪፖርቶች ተዘጋጅተዋል። በሁለቱም ክልሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር ምክክር ተደርጓል፤ ለምክረ ሐሳቦቹ ተፈጻሚነት የውትወታ ሥራ ተሠርቷል። በሪፖርት ዘመኑ የምክረ ሐሳቦች አተገባበር ክትትል የተከናወነ ሲሆን ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከተጎጂ ማኅበረሰብ መረጃዎችን በማሰባሰብ የክትትሉ የመጨረሻ ሪፖርት ይፋ ሆኗል።

- ለ73ኛው እና 75ኛው የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን መድረክ የሚቀርብ የሀገሪቱን የኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች ሁኔታ የሚዳስስ እንዲሁም መብቶቹን በሚመለከት የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን ምክረ ሐሳቦችን የያዙ ጽሑፎች ተዘጋጅቷል። ለ73ኛው እና 75ኛው የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን መድረክ ቀርቧል።

- የግል ሥራ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሠራተኞች መብቶች አተገባበር ዙሪያ በአዲስ አበባ፣ በባሕር ዳር፣ በሃዋሳ እና በጅማ ከተሞች የተካሄደ የክትትል ሥራ የመጨረሻ ሪፖርት ይፋ ተደርጓል። በግኝቶቹ እና በምክረ ሐሳቦቹ ላይም ጥናት በተደረገባቸው ከተሞች የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተዋል።

- የግል ጤና ዘርፍ የፋይናንስ ተደራሽነት ላይ ያተኮረና የጤና መብት አተገባበርን ለመገምገም ያለመ የክትትል ሥራ በአዲስ አበባ፣ በባሕር ዳር፣ በሃዋሳ፣ በጅማ እና በጅግጅጋ ከተሞች ተከናውኗል። የክትትል ሪፖርቱ ውጤት ላይም የጥናት ዘርፉ



ከሚመለከታች ባለድርሻ አካላት ጋር በየከተሞቹ ምክክር ተካሂዷል።

- ከመገናኛ ብዙኃን ለቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎችና ለኅብረተሰቡ በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች እና በዘላቂ ልማት ግቦች ላይ መልእክት ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ዘጠኝ የሬዲዮ እና አራት የቴልቪዥን ቃለ መጠይቆች ተደርገዋል።

- በኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ውስጥ ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የሥራ ሁኔታዎችን የማግኘት መብት አተገባበር ላይ የክትትል ሥራ ተከናውኗል።

- የኢመደበኛ አሰፋፈር አካባቢ ላይ የሚኖሩ ሰዎች በቂ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ የምርምር ረቂቅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

- ከGIZ-PILUP II Project ጋር በመተባበር ሰብአዊ መብቶች እና የመሬት መብቶች በሚል ርዕስ የባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ እና የውትወታ መድረክ በሥራ ክፍሉ የተዘጋጀ ሲሆን በመድረኩም በሥራ ክፍሉ 3 ጹሁፎች ቀርበዋል።

- ከታች በተገለጹት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተጀመሩ የምርምር ሥራዎች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።

    - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለሦስት እና አራት እግር (ባጃጅ) አነስተኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተሽከርካሪዎች ላይ ያስቀመጠውን እገዳ አስመልክቶ የሚካሄድ ምርመራ፣

    - በሸገር እና አዲስ አበባ ከተሞች እየተካሄደ በሚገኘው ቤቶችን የማፍረስ እና በግዳጅ የማስነሳት እርምጃ ላይ ምርመራ፣

    - በማኅበራዊ ዋስትና መብት ላይ የሕግ ማዕቀፎችንና አተገባበራቸውን ለመፈተሽ የሚያስችል ምርምራ

- ከተለያዩ አካላት ጋር በመተባበር 3 የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የምክክር መድረኮች

ተዘጋጅተዋል። ለውይይት መድረኮቹ መነሻ ጽሑፎች ተዘጋጅተዋል።

- የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሁኔታ ዘገባ (Situation Report) በሥራ ክፍሉ ተዘጋጅቷል። ረቂቁ ተገምግሞ ለዘርፉ ኮሚሽነር ተልኳል።
- በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ዙሪያ በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የተሰጡ የውሳኔ ሃሳቦችንና ጠቅላላ አስተያየቶችን ተደራሽ ለማድረግና ለሚመለከታቸዉ የመንግሥት አካላት ለማሳወቅ ይረዳ ዘንድ በአማካሪ ድርጅቶች ተተርጉመው በቀረቡ ሰነዶች ላይ በሥራ ክፍሉ ባለሞያዎች ሙያዊ አስተያየት ተሰጠባቸዋል። በዚህም መሠረት በተ.መ.ድ. የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች ኮሚቴ፦
  - በቂ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት ላይ የሰጠው አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 4፣
  - በቂ መኖሪያ የማግኘት መብት (ከመኖሪያ ቦታ ማፈናቀል) ላይ የተሰጠ አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 7 (1997 እ.ኤ.አ)፣
  - የሥራ መብትን አስመልክቶ የተሰጠ አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 18፣
  - ፍትሐዊ እና አመቺ የሥራ ሁኔታዎች የማግኘት መብትን በተመለከተ የተሰጠ አጠቃላይ ትንታኔ ቁጥር 23 (እ.ኤ.አ 2016); ተተርጉመው ታትመዋል።

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- የኮሚሽኑን ሪፖርትና ውትወታ ተከትሎ በአዲስ አበባ እና በዙሪያዋ ወደ 7,000 የሚጠጉ ባለ ሶስት ጎማ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ሰጪዎችና ነዋሪዎች እንቅስቃሴ ላይ የተጣለው እገዳ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተነስቷል። መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም የምርመራውን ውጤት እና የውሳኔ ሃሳቦች ለባለድርሻ አካላት እና ለኅብረተሰቡ በሰፊው ተደራሽ አድርጎታል።
- በኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መብቶች ሕጎች/ፖሊሲ ከሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎች አንጻር ያለባቸው ክፍተቶች ተለይተው እንዲታረሙ ምክረ ሐሳቦች ቀርበዋል።
- በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች ዙሪያ በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የተሰጡ የውሳኔ ሐሳቦችን አፈጻጸም ላይ ያሉ ክፍተቶች ተለይተዋል፣ የማስተካከይ ምክረ ሐሳብ ተሰጥቷል።
- የመብት ባለቤቶች እና ባለግዴታዎች በኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ መብቶች ላይ ያላቸው ዕውቀት እንዲዳብር ተደርጓል።

## 3.8. ኮሙኒኬሽን ኢ.ኮ.ቴ እና አጋርነት

### 3.8.1. ሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን

#### የተከናወኑ ተግባራት

- የኮሚሽኑን የድምጸ መስል ዝገጅት እና ዲዛይንን ጨምሮ ሁሉንም የግንኙነት ሥራዎች ይመራል፣ ይቆጣጠራል:: የኹነት ዘገባዎች (Event Updates)፣ ዜና መግለጫዎች፣ የክትትልና ምርመራ ሪፖርቶች፣ የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ማብራሪያዎች፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች፣ ድንጋጌዎች፣ አዋጆች እና የትንታኔ ሰነዶች በኮሚሽኑ ድረገጽ እና ማኅበራዊ ሚዲያዎች ለሕዝብ ይፋ ተደርገዋል፣ ተሠራጭተዋል::

- ኮሚሽኑ ከሀገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ አጋር ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት የሚመጡ እንግዶችን ለማስተናገድ የተዘጋጁ ስብሰባዎችን እና ጉብኝቶችን አሰተባብሯል:: ተቋማዊ ቪዚቢሊቲን የሚያሳድጉ ሥራዎች ተከናውነዋል::

- የኮሚሽኑ ድረገጽ ሌሎች የግንኙነት መንገዶች የሚሰጡት አገልግሎት እንዳይቋረጥና ለጥቃት እንዳይጋለጡ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል:: የመከላከያ እርምጃዎች ተወስደዋል::

- ከ62 በላይ ከሚሆኑ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነት ተፈጥሯል::

- የውስጥ ኮሙኒኬሽ ከማጠናከር አንጻር የተከናወኑ ተግባራት:-
  - የ261 ዕለታዊ የሰብአዊ መብቶች ነክ ዜናዎች ዳሰሳዎች (Media Review) ጥንቅር፣
  - 12 ወርሃዊ እና 42 ሳምንታዊ ዲጂታል መጽሔቶች፣ እና
  - 10 ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች የሕግ ማዕቀፎች ማብራሪያ ሰነዶች ተዘጋጅተው ለሁሉም ሠራተኞች በኤ-መልዕክት (e-mail) ተሠራጭተዋል::

- የኮሚሽኑን የሥራ ክፍሎች እና ባለሙያዎች ሥራዎቻቸውን እና ልምዶቻቸውን ለባልደረቦቻቸው የሚያካፍሉባቸው 4 የኢሰመኮ ምሳዎች መርኃ ግብሮች ተዘጋጅተዋል::

- የከተማ ጽ/ቤቶች መረጃ የሚለዋወጡባችው 28 ሳምንታዊ የከተማ ጽ/ቤት ዜናዎች ተዘጋጅተው ተሠራጭተዋል::

- በኮሚሽኑ በየትኛውም ዘርፍ የሚዘጋጁ ሰነዶች ወጥ ቅርጽ፣ ይዘት እና የቃላት አጠቃቀም እንዲኖራቸው እና የሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ሥራን መምራት የሚያስችሉ የሥራ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል:: እንዚህ ሰነዶች ለሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ሥራ እንደ መመሪያ ያገለግላሉ::

- የድምጸ-ምስል (Audiovissual) ቡድን ተደራጅቷል:: ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች ጋር በመተባበር የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች እና ተቋማዊ የውስጥ ኮሙኒኬሽን ላይ ትኩረት ያደረጉ ከ20 በላይ የድምጸ-ምስል ውጤቶች ተዘጋጅተው ተሠራጭተዋል::

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- ኮሚሽኑ የሚያመነጫቸው ሰነዶችና መረጃዎች ይፋ ከመደረጋቸው በፊት ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ በድረገጽ እና በማኅበራዊ ሚዲያዎች ደኅንነታቸው ተብቆ ተደራሽ ሆነዋል፡፡
- የኮሚሽኑ ሥራ ውጤቶች በዓለም አቀፍ እና በሀገራዊ መገናኛ ብዙኃን እና በሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚያገኙት የዘገባ ሽፋን ጨምሯል
- በኮሚሽኑ የሚዘጋጁ ሪፖርቶች፣ መግለጫዎች፣ እና ሌሎች ሰነዶች ወጥ/ተመሳሳይ በሆነ ቅርጽና ይዘት እንዲሁም የፊደላት አጠቃቀም ያላቸው ሆነዋል፡፡
- የኮሚሽኑ የሥራ ውጤቶች ለመገናኛ በዙኃን እና ለሕዝቡ በቋሚነት የሰብአዊ መብቶች መረጃ ምንጭ ሆነዋል፡፡
- ሠራተኞች ወቅታዊ የሰብአዊ መብቶች መረጃ ያላቸው ሆነዋል፡፡
- የተቋማዊ ውስጣዊ ተግባቦት ዳብሯል፡፡

## 3.8.2. ኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ

### የተከናወኑ ተግባራት

- በመረጃ ቴክኖሎጂ የዘመነ የአቤቱታ መቀበያ እና መተንተኛ ሥርዓት በተሟላ መልኩ ተዘጋጅቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
- ዘመናዊ ነጻ የስልክ ጥሪ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች አቤቱታ መቀበያና ማስተናገጃ ሥርዓት ተከላ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡
- ‘ሌንስ’ በመባል የሚታወቅ የበለጸገ የዕውቀት ማከማቻ ዳታቤዝ ተዘጋጅቷል፡፡ በዳታቤዙ ተሞክሮዎች፣ ልምዶች እና ሰዶች ተመዝግበው የመረጃ ቋት ውስጥ ገብተዋል፡፡ የኮሚሽኑ ሠራተኞች ሌንስ ዳታ ቤዝን በመጠቀም የተከማቹ ሰነዶችና ተሞክሮዎችን በቀላሉ ማግኘት ችለዋል፡፡
- የድጋፍ አስተዳደር ሥርዓት ፍላጎትን በመገምገም አዲስ የሶፌትዌር ሥርዓት ግዥ ለመፈጸም የሚያስችል ስፔሲፊኬሽን እና የጨረታ ስነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ፍላጎት በመገምገም የሶፌትዌር ግዥ እና ጨረታ ሂደት የሚመራ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ እየተዘጋጀ ነው፡፡
- የኮሚሽኑ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች ላይ ግምገማ ተደርጓል፡፡ በዚህ ግምገማ መሠረት የቴክኖሎጂ ለውጥ ውስጥ ለኮሚሽኑ ሥራ የተሻለ ተስማሚ አጋር ለማግኘት ጋር ግምገማ ተካሂዶ ክላውድ ፕሮዳክቲቪቲ ከተባለ የማይክሮ ሶፍት የምሥራቅ አፍሪካ ወኪል ከሆነ ድርጅት ጋር ውል በመፈራረም ሥራው ተጀምሯል፡፡ የኮሚሽኑ የከተማ ጽ/ቤቶችን ጨምሮ ድርጅቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ማይክሮሶፍት ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሥርዓት የማሸጋገር ሥራ ተከናውኗል፡፡
- በዳታ ሴንተር የሚገኙትን የመረጃ ቋት 24/7 ተደራሽ እንዲሆኑ ለማስቻል ያለውን የመብራት ኀይል መቆራረጥ ለመከላከል ሁለት ባለ ከፍተኛ ጉልበት ዩፒኤሶች ግዢ ተከናውኗል፡፡ የገጠማው ሥራ በቀጣይ ሩብ ዓመት የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡
- በሁሉም የከተማ ጽ/ቤቶች የአይቲ ቁሳቁሶችን ግዥ እና የአይቲ ድጋፍ ፍላጎት መለያ የዳሰሳ ጥናት በመከናወን ላይ ነው፡፡
- የዳታ ሴንተር የማቋቋምና የኔትዎርክ ዝርጋታ ሥራ ተሠርቷል፡፡
- ሁሉንም የከተማ ጽ/ቤቶች ከዋናው መ/ቤት ጋር በዲጅታል ቴክኖሎጂ ለማስተሳሰር የቪፒኤን ሰርቨር በከተማ ጽ/ቤቶች የሚገኙ ሠራተኞችን ከዋናው መ/ቤት ጋር እንዲገናኙ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡
- የአይቲ አገልግሎት ድጋፎችን ለሚጠይቁ ሠራተኞች ሙያዊ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

### የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- በመረጃ ቴክኖሎጀ የዘመነ የአቤቱታ መቀበያ እና መተንተኛ ሥርዓትን በአግባቡ መጠቀም ተችሏል፡፡
- በዘመናዊ ነጻ የስልክ ጥሪ ማስተናገጃ ሥርዓት አማካኝነት የአቤቱታ መቀበያና ማስተናገጃ ሥርዓቱ ለሰዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሁም በጥሪ ቆይታ ጊዜ ስለ ኮሚሽኑ አገልግሎት አሰጣጥ መረጃ የሚሰጥ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- የበለጸገ የዕውቀት ማከማቻ ዳታቤዝ ተዘጋጅቷል፣ ተሞክሮዎች ተሰንደዋል፣ ትምህርቶችና ተሞክሮዎች ተመዝግበው የመረጃ ቋት ውስጥ ገብተዋል፣ ተ ሠራጭተዋል፣ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡
- ለሁሉም ሠራተኞች የኢሜል አገልግሎት እንዲኖራቸው በመደረጉ ለተሳለጠ ግንኙነት አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ ሠራተኞች በተቀላጠፌ እና በተሻለ ተቀራርበው እንዲሠሩ ማድረግ አስችሏል፡፡
- ሠራተኞች የአይቲ አገልግሎት ድጋፎች ያለምንም ችግር ማግኘት ችለዋል፡፡
- የዘመነ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ማስቻል እና የኮሚሽኑን መረጃ በአግባቡ መሰነድ ተችሏል፡፡

## 3.8.3. ፕሮግራምና አጋርነት










### የተከናወኑ ተግባራት

- ኮሚሽኑ ተልዕኮውን መወጣት የሚያስቸለውን የፋይናንስ የዕውቀትና የቁሳቁስ ድጋፍ ለማግኘት ከአጋር አካላት ማለትም ከአውሮፓ ኅብረት (EU)፤ ዳኒሽ የዴንማርክ የሰብአዊ መብቶች ተቋም (DIHR)፣ ከዩኒሴፍ (Unicef)፣ ሴቭ ዘቺልድረን (Save the Children) አጋር ድርጅቶች እና ከአይሪሽ ኤይድ (Irish Aid) ጋር የሁለትዮሽ እና የሦስትዮሽ የትብብርና የድጋፍ ስምምነት ተፈርሟል፡፡

- የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ለኮሚሽኑ በማማከር እንዲሠሩ የተለያየ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችን ያካተተ አማካሪ ቡድን ተቋቁሟል፡፡ የኪነ-ጥበብ አማካሪ ሚናን ማሳደግ፣ የተከናወኑ የኪነ- ጥበብ ሥራ ውጤቶች ሰብአዊ መብቶች ከማስፋፋት ማኅበረሰብ ማነቃነቅ እንዴት መጠቀም ይቻላል በሚሉ ርዕሶች በኮሚሽኑ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት ክፍል በኩል የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ቀርቦ ተጨማሪ ግብአት ለማሰባብሰብ የሚያስችል ውይይት ተደርጓል፡፡

- የሰብአዊ መብቶች እሴቶች ላይ ያተኮረ በተለያዩ የኪነ-ጥበብ ዘርፎች የተሰማሩ ባለሙያዎች የተሳታፉበት የኪነ ጥበብ አማካሪ ሚናን ማሳደግ፣ የተከናወኑ የኪነ ጥበብ ሥራ ውጤቶች ሰብአዊ መብቶችን ለማስፋፋትና ማኅበረሰብ ለማነቃነቅ እንዴት መጠቀም ይቻላል በሚሉ ርዕሶች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተካሂደዋል፡፡

- ከስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና የፍልሰተኞች መብቶች የሥራ ክፍል እና ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች ኅብረት (CEHRO) ጋር በመተባበር ኅዳር 2 ቀን 2015 ዓ.ም. የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል፡፡

- ኢሰመኮ ታኅሣሥ 1 ቀን የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቀንን በማስመልከት ለሁለተኛ ጊዜ ዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል ከታኅሣሥ 1 እስከ 20 ባሉ ቀናት ተዘጋጅቷል፡፡ በፊልም ፌስቲቫሉ አሥራ አምስት የሚሆኑ አጫጭርና ዘጋቢ የሀገር ውስጥና የውጭ ፊልሞች የተመረጡ ሲሆኑ ፌስቲቫሉ የተካሄደባቸው ከተሞች አዲስ አበባ፣አዳማ፣ ባሕርዳር፣ ጅግጅጋ እና ሃዋሳ ናቸው፡፡

- ቅሬታ አቅራቢ ባለጉዳዮች እና ለመብት ጥሰት ተጎጂዎች የተሟላ መፍትሔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ተጓዳኝ አገልግሎት ከሚሰጡ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር የአገልግሎት ቅብብሎሽ ሥርዓት (Referral System) ለመዘርጋት ከባለድርሻ አካላት ጋር የመጀመሪያ የምክክር መድረክ ተደርጓል።

- በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ለሚያልፉ ሰዎች የሚሰጠው ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ጥራት እና ተደራሽነት ላይ ያተኮረ ሀገር አቀፍ ውይይት ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር እና የክልል መሥሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ማእከላት፣ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበራት እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር አካሂዷል።

- የፕሮጀክቶች ወቅታዊ አፈጻጸም ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ከድጋፍ ሰጪ አካላት እና ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል።

- ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲሁም የፕሮጀክት ፋይናንስ ድጋፍ ለሚሰጡ አጋር ድርጅቶች መቅረብ ያለባቸው ዕቅዶችና የአፈጻጸም ሪፖርቶች በሙሉ ወቅቱን ጠብቀው እንዲዘጋጁና እንዲቀርቡ ተደርጓል።

- ለሦስት የኮሚሽኑ የሥራ ክፍሎች ከ5 ዓመቱ ስትራቴጂ ዕቅዱ ጋር ትይዩ የሆነ ንዑስ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ለውይይት ቀርቧል።

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- ኮሚሽኑ ተልዕኮውን መወጣት የሚያስችለውን የፋይናንስ የዕውቀትና የቁሳቁስ ድጋፍ ከአጋር አካላት አግኝቷል።
- የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችን በሰብአዊ መብቶች እሴቶች ዙሪያ ግንዛቤያቸውን ማሳደግና የሲቪል ማኅበራት ከኮሚሽኑ ጋር ተባብሮ መሥራትን አጎልብቷል።.
- የአጋር ድርጅቶች ሚና ለማሳደግ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እና ተግባራዊ ምላሽ እንዲኖረው ተጽዕኖ ለማምጣት የሚያስችሉ የውትወታ ሥራዎች በጋራ ለመሥራት መግባባት ላይ ተደርሷል።
- የሚሰጡት አገልግሎት ዓይነትና የድርጅቶች የቅብብሎሽ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተለይተዋል።
- በዓመታዊ የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል በሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ግንዛቤ ማስጨበጥ ተችሏል።
- የአጋርነት ስትራቴጂክ መመሪያ ተዘጋጅቷል።
- በሕግ ድጋፍ አገልግሎት ተደራሽነት እና ጥራት ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ለማስተካከል የተግባር እቅድ ተዘጋጅቷል።
- አዲስ አበባ ከሚገኙ ፈቃደኛ አጋር ድርጅቶች ጋር የቅብብሎሽ ሥራዎች ተጀምሯል።
- ኮሚሽኑ ነጻና ገለልተኛ ተቋም በመሆኑ የተለያዩ የልማት አጋሮች ድጋፍ እንዲያደረጉ ዕድል ፈጥሯል።

## 3.9. ተቋማዊ ሪፎርም፣ ዐቅም ግንባታና ቀጣይነት

### 3.9.1. ዋና ኮሚሽነር ጽ/ቤት

#### የተከናወኑ ተግባራት

- አግባብ በሆኑ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ጉባኤዎች ተሳትፎ:-
  - በተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት 51ኛው እና 52ኛው መደበኛ ጉባኤዎች በመሳተፍ የኢትዮጵያን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የተመለከተ ሪፖርት ቀርቧል።
  - ኮሚሽኑ በብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ዓለም አቀፍ ጥምረት (Global Alliance of National Human Rights Institutions/GANHRI) ዓመታዊ ጉባኤ ላይ ተሳትፏል።
  - በ73ኛው የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን (African Commission on Human and Peoples' Rights) መደበኛ ጉባኤ ላይ ኢሰመኮ ተሳትፏል።

- ለዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ሂደቶች/ተቋማት/ ማዕቀፎች በኢትዮጵያ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የሚመለከቱ በጥቅሉ ስድስት ሪፖርቶችን በመላክ በኢትዮጵያ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለነዚህ አካላት ማስገንዘብ ተችሏል።

- በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን እና በአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት የባለሞያዎች ኮሚቴ የአጋርነት ዕውቅና (observer status) ለማግኘት በሚቀርበው ጥያቄ ዙሪያ ለሲቪል ማኅበራት ግንዛቤ ለመፍጠር የአንድ ቀን ዐውደ ጥናት ተካሂዷል።

- በተጨማሪም ከአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ፍርድ ቤት (African Court on Human and Peoples' Rights) ጋር በመተባበር በፍርድ ቤቱ ሥልጣን፣ ሥራና ከፍርድ ቤቱ ጋር ለመሥራት ያሉትን ዕድሎች አስመልክቶ ለኢሰመኮ ባልደረቦችና ለሲቪል ማኅበራት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

- ኢሰመኮ ከአፍሪካ ፍርድ ቤት ጋር በመተባበር ኢትዮጵያ የአፍሪካ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ ፕሮቶኮልን የምታጸድቅበት ሁኔታን አስመልክቶ ውይይት የተደረገበት እና በፍርድ ቤቱ ሥራና ሥልጣን ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠርን ያለመ ሴሚናር አዘጋጅቷል።

- ከተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት የምሥራቅ አፍሪካ ቢሮ (OHCHR-EARO) እና ከአፍሪካ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ኔትወርክ (Network of the African National Human Rights Institutions/NANHRI) ጋር በመተባበር በሀገር ውስጥ ፍርድ ቤቶችና በአህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስልቶች በሚካሄደው ስልታዊ ሙግት ላይ ለሲቪል ማኅበራት ዐውደ ጥናት ተዘጋጅቷል።

- በጳጉሜ 4 ቀን 2014 ዓ.ም. የተከበረውን የአፍሪካ ኅብረት ቀንን አስመልክቶ ኢሰመኮ መልእክት በማስተላለፍ በቀኑ ዙሪያ ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ ፈጥሯል።

- የሰብአዊ መብት ጥሰት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራ ፅንሰ ሐሳብ የሚያስረዳ ሰነድ እንዲሁም የቅድመ ማስጠንቀቂያ ተግባር የሥራ ሂደትን የሚተነትኑ ሁለት ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። ሰነዶቹን ለማዘጋጀት እንዲያስችል ጉዳዩን የሚመለከቱ ሰነዶች ተመርምረዋል እንዲሁም በሥራው ላይ ካሉ ባለሙያዎች ጋር ውይይት ተደርጓል።

- ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር የምሥራቅ አፍሪካ ጽ/ቤት (UNOHCHR — EARO) ጋር በመተባበር በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት ጉዳት ከደረሰባቸውና ተጋላጭ

የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ ከሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ በሰላም እና ጸጥታ ላይ ከሚሠሩ የሲቪል ማኅበራት፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት መሪዎች ጋር የሽግግር ፍትሕን በተመለከተ 15 የመስክ ምክክሮች ተደርገዋል።

- የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማዕቀፍን ለማዳበር ይረዳሉ የተባሉ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክረ ሐሳቦች፣ እንዲሁም የፖሊሲ ማዕቀፍን በመንደፍም ሆነም በመተግበር ሂደት ውስጥ በአትኩሮት ሊጤኑ የሚገባቸው ዓለም አቀፍ መርሖችን ያካተተ መሪ ሰነድ (Advisory Document) ተዘጋጅቶ ይፋ ተደርጓል።
- በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፍትሕ ሚኒስቴር ሥር ለተቋቋመው ከፍተኛ የባለሙዎች ቡድን የተለያዩ የቴክኒክ እና የምክር ድጋፎችን ሰጥቷል። በሽግግር ፍትሕ ዙሪያ ከሚሠሩ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ተቋማት እንዲሁም የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ጋር አጋርነትን በመፍጠር ረገድ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። የሽግግር ፍትሕ ከፍተኛ የባለሞያዎች ቡድን የሚያከናውናቸው የሕዝባዊ ምክክሮች ላይ ክትትል ተደርጓል።
- የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ለመሰነድ እንዲችሉ ለዘርፍ ክፍሎች እና የከተማ ቢሮዎች ድጋፍ እና ክትትል ተደርጓል። የዘርፍ ክፍሎችን ዘገባ በማሰባሰብ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።
- መንግሥታዊና አማራጭ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን አዘገጃጀት አስመልክቶ ለመንግሥት አካላት፣ ሲቪል ማኅበረሰብ፣ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ስልጠናዎች ተሰጥቷል።

## የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- ለዓለም አቀፍና ለአህጉራዊ የሰብአዊ መብት ሂደቶች/ተቋማት ማዕቀፎች በኢትዮጵያ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ማስረዳት ተችሏል።
- በዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ሂደቶች/ተቋማት ሕዝባዊ ጉባኤዎች የኢሰመኮ ትርጉም ያለው ተሳትፎ አጠናክሯል።
- የአጋርነት ዕውቅና (observer status) ለማግኘት በሚቀርበው ጥያቄ ዙሪያ የሲቪል ማኅበራት ግንዛቤ አድጓል።
- በሽግግር ፍትሕ ፅንሰ ሐሳቦች እና አማራጮች ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ ተፈጥሯል።
- በሽግግር ወቅት የሚደረግ የፍትሕ ሂደትን የሚያግዙ ማኅበረሰባዊ እሴቶች ተለይተዋል፤ የተጎጅዎች ምኞት እና ፍላጎት ተሰንዷል።
- በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትሕ ላይ መሪ ሰነድ (advisory document) ተዘጋጅቷል።
- በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፍትሕ ሚኒስቴር ሥር የተቋቋመው ከፍተኛ የባለሙዎች ቡድን የተለያዩ የቴክኒክ እና የምክር ድጋፎችን አግኝቷል።
- በአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ፍርድ ቤት ሥልጣን፣ ሥራና ከፍርድ ቤቱ ጋር ለመሥራት ባሉ ዕድሎች ዙሪያ ለኢሰመኮ ባልደረቦች እና ለሲቪል ማኅበራት ግንዛቤ ተፈጥሯል።
- ለመንግሥት አካላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ስለ አፍሪካ የሰብአዊ መብቶች ፍርድ ቤት እና የፍርድ ቤቱን ማቋቋሚያ ፕሮቶኮል ማጽደቅ ስለሚኖረው ጥቅም ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።

## 3.9.2. የፋይናንስ እና አስተዳደር

### የተከናወኑ ተግባራት

- ምቹ የሥራ ቦታን እና የከተማ ጽ/ቤቶችን ተደራሽነት ለማመቻቸት በባሕር ዳር፣ በጅማ እና በጋምቤላ ጽ/ቤት አዲስ ቢሮ የማደራጀት ሥራ ተሠርቷል፡፡ የጅግጅጋ፣ ሃዋሳና ሰመራ ጽ/ቤቶችን በአዳዲስ የቢሮ ዕቃዎች ለማደራጀት ኮሚሽኑ ባወጣው የቢሮ አደረጃጀት ስታንዳርዳይዜሽን መሠረት ጥናት ተሠርቶ ግዥው በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

- በሁሉም ጽ/ቤቶች ለአንድ ዓመት አስፈላጊ የሆኑ የቢሮ ቁሳቁሶች እና ለመስተንግዶ የሚፈለጉ ዕቃዎች ተገዝተዋል፤ ተሠራጭተዋል፤ ሥራ ላይ ውለዋል፡፡

- የፋይናንስ አሠራርና ቁጥጥርን ለማሻሻል፡-
    - Electronic Government Procurement (E-GP) ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና ባለሞያዎች ሰልጥነዋል፡፡ የ2016 ዓ.ም. በጀት ዓመት የግዥ ዕቅድ በሲስተሙ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡
    - የፋይናንስ፣ ግዥ፣ በጀት፣ የንብረት አስተዳደር፣ የውስጥ ኦዲት አስተዳደር ፖሊሲ ማንዋል ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ በኮሚሽነሮች ጉባኤ ጸደቆ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፣ ለሚመለከታቸው 50 የኮሚሽኑ ሠራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
    - የፕሮጀክቶች ዝርዝር ተግባራት በኢፍሚስ (IFMIS) ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ሪፖርቶች ወጥ እንዲሆኑ እና ጥራት ያለው ቀልጣፋ ሥራ እንዲኖር ተደርጓል፡፡
    - በIFMIS አጠቃቀም ዙርያ 10 ለሚሆኑ የሚመለከታቸው የፋይናንስ ባለሞያዎች ከገንዘብ ሚንስቴር ጋር በመተባበር የ10 ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
    - በሁሉም ጽ/ቤቶች የዘመናዊ ክፍያ (e-Payment) ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡
    - ከድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች የተገኙ አስር ተጨማሪ ተሽከርካሪዎች ፎርማሊቲውን አሟልተው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡
    - ፋይናንስና አስተዳደር ሥራ ክፍል የሚያስፈልግውን የሰው ኃይል 90% ማሟላት ተችሏል፡፡

- የአጋር ድርጅቶች የፋይናንስ ድጋፍ አጠቃቀም በውስጥና በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ቀርቧል፡፡

- የከተማ ጽ/ቤቶች የመደበኛ እና የፕሮጀክት የፋይናንስ አጠቃቀም በውስጥ ኦዲተር ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቀርቧል፤ ለገንዘብ ሚኒስቴርም ተልኳል፡፡

- የ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት መደበኛ በጀት ሪፖርትን በተመለከተ የኢሰመኮ የ2014 መደበኛ በጀት አጠቃቀም በፌዴራል ዋና ኦዲተር ምርመራ ተጠናቆ የኦዲት ውጤቱም በአጥጋቢ ሁኔታ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

## 3.9.3. የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር

### የተከናወኑ ተግባራት

- የኮሚሽኑን ከፍተኛ አመራር ብቃት ለማጎልበት የሚረዳ የሦስት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በሰው ሀብት ዕቅዱ መሠረት ለክፍት የሥራ መደቦች በተገቢው ሰዓት፣ የጥራት ደረጃ እና ብዝኀነትን ባማከለ ሁኔታ ሁሉም ሥራ ክፍሎች በቂ የሆነ የሰው ሀብት እንዲኖራቸው ቅጥር ተፈጽሟል፡፡
- የሠራተኞች መረጃ በሰው ሀብት መረጃ ሥርዓት (HRIS) ተደራጅቷል፡፡
- ሠራተኞችን በኮሚሽኑ ለማቆየት የሚያስችል የስትራቴጂ ዕቅድ ተነድፎ በትግበራ ላይ ይገኛል፡፡
- የሠራተኞችን የመፈጸም ዐቅም በተከታታይነት ለማጎልበት የሚያስችል እና በኮሚሽኑ የሰው ሀብት መመሪያ መሠረት የተዘጋጀ አዲስ የሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም መመሪያ እና መርኃ ግብር ተዘጋጅቶ ለሁሉም የሥራ ክፍሎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የሠራተኞች መረጃ ትንተና ሪፖርት ለማዘጋጀት የሚያስችል የሰው ሀብት መረጃ ስርዓት (HRIS) በሠራተኞች ምረጃ ተደራጅቷል፡፡
- ለአዳዲስ ሠራተኞች ውጤታማ የሆነ የሠራተኞች ትውውቅ (induction) ፕሮግራም ለማዘጋጀት የሚረዳ የትውውቅ ፕሮግራም የአሠራር ሥርዓትን የሚያሳይ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- የኮሚሽኑን ሠራተኞች እርካታ እና ተቋማዊ ባህል ዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡

### የተገኙ ዐበይት ውጤቶች

- ኮሚሽኑ ዕቅዱን ለማሳካት የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል አለው፡፡
- የኮሚሽኑ መካከለኛ አመራር ዐቅም በተወሰነ ደረጃ ጎልብቷል፡፡
- የሰው ሀብት መረጃ ሥርዓት (HRIS) መሠረታዊና ወቅታዊ የሠራተኞች መረጃ ትንተና ሪፖርት ለማዘጋጀት አስችሏል፡፡ የአሠራር ቅልጥፍና አድጓል፡፡
- በመርኃ ግብሩ መሠረት 90% የሚሆኑት የኮሚሽኑ ሠራተኞች የግለሰብ የልማት ዕቅድን ጨምሮ የሥራ ዕቅድ ማዘጋጀት ችለዋል፡፡
- ተቋሙን የሚቀላቀሉ አዳዲስ ሠራተኞች የኮሚሽኑን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ስትራቴጂ ዕቅድ፣ የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን ዕቅድ እና የራሳቸውን ኃላፊነት ተገንዝበዋል እና በሥራቸው ውጤታማ ሆነዋል፡፡

# 4. የሪፖርት ዘመኑ የበጀት ዕቅድ አፈጻጸም ማጠቃለ

ኮሚሽኑ ከመንግሥት በሚመደብለት የመደበኛ በጀትና ከአጋር ድርጅቶች በተገኘ ድጋፍ በ2015 በጀት ዓመት የተለያዩ ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን በሪፖርት ዘመኑ የታየው የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረዦች ተመልክቷል፡፡

**የ2015 በጀት ዓመት (ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም. - ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም.) የመደበኛ በጀት አፈጻጸም ሪፖርት**

| ተ.ቁ | መ/ቤት | ለ2015 የጸደቀ በጀት (በብር) | በ2015 በጀት ዓመት ሥራ ላይ የዋለ በጀት (በብር) | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| | | በመንግሥት | በመንግሥት | የዓመት አፈጻጸም በመቶኛ |
| 1 | ዋና መ/ቤት | 117,254,810 | 117,175,757 | 100% |
| 2 | ጋምቤላ | 6,593,350 | 6,494,618 | 99% |
| 3 | ባሕር ዳር | 9,225,360 | 8,982,330 | 97% |
| 4 | ጂማ | 9,328,581 | 9,098,433 | 98% |
| 5 | ጂግጂጋ | 5,611,600 | 5,532,322 | 99% |
| 6 | ሃዋሳ | 9,456,045 | 9,398,262 | 99% |
| 7 | ሰመራ | 5,236,691 | 5,206,414 | 99% |
| 8 | አሶሳ | 6,722,888 | 6,575,251 | 98% |
| | ለ2015 የጸደቀ በጀት ድምር | 169,429,324 | 168,463,387 | 99% |

**የ2015 በጀት ዓመት (ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም. - ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም.) የውጭ ፋይናንስ የጥሬ ገንዘብ አጠቃቀም**

| ተ.ቁ | የፋይናንስ ምንጭ | ገቢ በጀት | | | ሥራ ላይ የዋለ (ክንውን) | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከ2014 የዞር | ለዓመቱ የተለቀቀ | ድምር | በብር | አፈጻጸም በመቶኛ |
| | 1 | 2 | 3 | 4= 2 + 3 | 5 | 6= 5/4*100 |
| 1 | DIHR | 17,723,870 | 103,450,272 | 121,174,141 | 103,368,257.00 | 85% |
| 2 | UNICEF | 858,128 | 3,704,161 | 4,562,289 | 3,18,093.00 | 70% |
| 3 | IRISH AID | 23,129,677 | 31,577,773 | 54,707,450 | 29,572,251.00 | 54% |
| 4 | EU | 3,434,601 | 26,143,620 | 29,578,221 | 27,190,589.00 | 92% |
| 5 | OSIEA | 8,200,751 | | 8,200,751 | 8,200,751.00 | 100% |
| 6 | SCI | | 2,838,386 | 2,838,386 | 2,898,922.73.00 | 102% |
| 7 | UNCHR | 2,400,000 | 3,692,707 | 6,092,707 | 6,092,707.00 | 100% |
| 8 | SIWZERLAND EMBASSY | | 1,499,333 | 1,499,333 | 1,499,333.00 | 100% |
| 9 | EU/DIHR | | 27,587,030 | 27,587,030 | 13,047,946.00 | 47% |
| 10 | GDPP | | | | 573,904.86 | |
| | ድምር | 53,347,026 | 200,493,282 | 256,240,308 | 195,625,755.00 | 76% |

# 5. በአፈጻጸም ያጋጠሙ ችግሮች እና የማስተካከያ እርምጃዎች

- ስልጠናዎች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሚሰጡበት ወቅት ስልጠናዎቹ በአካባቢው ቋንቋ እና በምልክት ቋንቋ እንዲሰጡ እና የስልጠና መምርያዎችም ተተርጉመው እንዲቀርቡላቸው ከሰልጣኞች ጥያቄ የሚቀርብ መሆኑና ሁሉንም ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችል በቂ የቋንቋ ችሎታ ያለው የሰው ኃይል አለመኖሩ እንደ ክፍተት ተወስዷል፡፡ በተቻለ መጠን ስልጠናዎች የአካባቢውን ቋንቋ መናገር በሚችሉ የሥራ ክፍሉ ባለሙያዎች እንዲሰጡ በማድረግ ወይም አስተርጓሚዎችን በመጠቀም ችግሩን ለማቃለል ተሞክሯል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎችን በመጠቀም እንዲሁም ለዓይነ ሥውራን ሰልጣኝ-አሰልጣኞች የስልጠና መምርያዎችን በብሬል በማስተርጎም ችግሩን ለመፍታት ተሞክሯል፡፡

- ቀደም ሲል በተለይም በ2013 ዓ.ም. በተከናወኑ የስልጠና ተግባራት ላይ በቂ መረጃ ባለመኖሩ ምክንያት በመንፈቅ ዓመቱ የተከናወነውን የስልጠና ውጤታማነት ግምገማ በማከናወን ሂደት ባለድርሻዎችንና ሰልጣኞችን በቀላሉ ለማግኘት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ በተቻለ መጠን መረጃዎችን በተለያየ መንገድ ማለትም በስልክ፣ ወደተቋማቱ በአካል በመሄድ፣ ከተለያዩ አካላት መረጃ በማሰባሰብና በማጠያየቅ ለመፍታት ተሞክሯል፡፡

- በጋምቤላ ክልል በሁለተኛው ሩብ ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ሥራዎችን በተመለከተ በወቅቱ በኮሚሽኑ የጋምቤላ ቅርንጫፍ ቢሮ ላይ የደረሰው ጉዳት እና በባለሙያዎች ላይ የተፈጠረው ስጋት ዕቅዱን ከመፈጸም አንጻር እክል የፈጠረ ሲሆን ችግሩን ለማቃለል ለተወሰነ ጊዜ የመስክ ሥራ የሚጠይቁ ተግባራትን የማሻገር እና በሌሎች ለአደጋ በማያጋልጡ ተግባራት የመተካት ሥራ ተሠርቷል ፡፡

- የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች ክፍል የምክክር እና ትስስር መድረኮች ለማካሄድ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሆነ ሆቴል በበቂ ሁኔታ አለማግኘት ከገጠሙት ተግዳሮቶች አንዱ ነው፡፡ ይህንን ለመቅረፍ የአካባቢ ተደራሽነትን የማረጋገጫ ዝርዝር (checklist) በመጠቀም ስብሰባ በሚከናወንባቸው ሆቴሎች ተደራሽነት ዙሪያ ግምገማ አድርጓል፡፡

- በአንዳንድ የሀገሪቱ ክልሎች በተከሰተው የጸጥታ ችግር ምክንያት የክትትል ሥራውን ማከናወን አለመቻል አንዱ ተግዳሮት ነው፡፡ ይህንን ለመፍታት ኮሚሽኑ መድረስ ያልቻለባቸው ቦታዎች ላይ ስልክ በመደወል እና በደብዳቤ ምላሽ በመጠየቅ በከፊል ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

- በአማካሪ በኩል የሚከናወኑ ሥራዎች መዘግየት ኮሚሽኑ ካጋጠሙት ተግዳሮቶች አንዱ ሲሆን ይህንንም ለመፍታት የማስረከቢያ ቀናትን በማስቀመጥና ከፍተኛ ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

- የክትትል እና የምርመራ ሥራዎችን በማድረግ ረገድ ከጸጥታ አካላት ዛቻ እና እንግልት መፈጠሩ፣ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት መረጃ ለመሥጠት ፍቃደኛ አለመሆን እና ማንገላታት በሥራ ሂደታችን ካጋጠሙን ተግዳሮቶች ዋናዎቹ ናቸው:: ይህን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው የክልል ከፍተኛ ባለሥልጣናት የትብብር ደብዳቤ እንዲጽፉልን ማድረግ

እና በተዋረድ በታችኛው የመንግሥት እርከን ላይ ያሉ አካላት ተባባሪ እንዲሆኑ መመሪያ እንዲሰጣቸው ተድርጓል፡፡

- የሰብአዊ መብት ጥሰት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራ አዲስ እንደመሆኑ ሥራው ያልዳበረ መሆኑ እና በተጨማሪም የልዩ ባለሙያ አለመኖር የሥራ አፈጻጸም በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይተገበር ምክንያት ሆኗል፡፡

- በሽግግር ፍትሕ ዙሪያ በተደረጉት የመስክ ምክክሮች በቂ የሴቶች ተሳትፎን ማረጋገጥ እንደ አንድ ችግር የሚወሰድ ነበር፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ በእያንዳንዱ የምክክር ቦታ ከ15 እስከ 20 የሚደርሱ ሴት ተሳታፊዎች እንዲኖሩ ተደርጓል፡፡ ሴት ተሳታፊዎች ከማንኛውም ግፊት ነጻ ሆነው ሐሳባቸውን እንዲገልጹ፤ ሴቶችን ብቻ ያካተተ የተመጠነ የቡድን ውይይቶች እንዲካሄዱ ተደርጓል፡፡

- ለኮሚሽኑ የሚመደበው የመንግሥት ግምጃ ቤት በጀት ውሱን በመሆኑ በሥራ አፈጻጸም ላይ የሀብት እጥረት ጫና ፈጥሯል፡፡